# የገብረመድህን ወግ

**ኢትዮጵያውያን (በተለይ አማሮች) ቢኖሩ አይጠቅሙንም - ቢጠፉም አይጎዱንም (1975፡ ሕወሀት)**



እየተጓዝኩ ነበር። ከቦታ ቦታ። ከቢሲ እስከ ዲሲ የታዘብኩትን፡ የከነከነኝን፡ ሆዴን የበላውን እጽፋለሁ እያልኩ ስዘገጃጅ፡ በዚህ መሀል ነው ገብሬን ሲናገር የሰማሁት። ገብረመድህን አርአያ። የሱ ወግ ጊዜ አልሰጠኝም። ሌላው ይቆይ። የቀድሞ የህወሀት አባልና ገንዘብ ቤትን ወግ ላወጋችሁ ፈቀድኩ። ሙያዬ ምስክር፡ ወይም ብዙ ወንድማገኘሁ አንዳንደዬ ልብ ሰቃይ ቅጽበቶች ላይ እየገባች ብስጭት ብታደርገኝም፡ እየጎረጎረች፡ እየሰረሰረች፡ ደግሞም እየፈለፈለች የምታወጣቸውና የምታናዝዛቸው ሰዎች ያስደስቱኛል። ባለፈው ቅዳሜ፡ ገብረመድህን አርአያ አስደሰተኝ። አስደመመኝ። አሳቀኝ። አሳዘነኝ። እንደወረደ ይናገራል። እንደመጣ ይሰይማል። ጣጣ የለውም። አብርሀም ያየህ እሱንም አበሳጭቶት ኖሮ ፡ "ዋይ፡ እሱ እኮ ጭልፊት ነው፡ ጭልፊት ታውቃላችሁ? ጭልፊት። ቆሻሻ ነው። ሌባ ነው። የማይረባ።" ለብቻዬ ነበር የምሰማው። ቤቴ እስኪታዘበኝ ሳቅኩኝ። ተንከተከትኩኝ። ሁለት ሶስት አራት በሳቅ የሚያንፈቀፍቁ ቅጽበቶች ነበሩ፤ በዚያ ባለፈው እሁድ፡ ኦገስት 23 ቀን በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ እንግዳ ሆኖ የቀረበው አቶ ገብረመድህን አርአያ በሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ።

ገብሬ ማነው? ገብረመድህን አርአያ የዛሬ 36 ዓመት ኣካባቢ ነው መንገድ ላይ ሲሄድ ወይንም እርሻውን ከሚያርስበት መጥተው የማገብት ሰዎች የያዙት። ማህበረ ገስግስቲ ብሄረ ትግራይ። ምንም የፖለቲካ እውቀት አልነበረኝም ይላል። ብሄር፡ ብሄረሰብ፡ ብሄረተኝነት፡ የብሄር ጭቆና ምናምን የሚባል ነገር አያውቅም ነበር። በዚያ ምንም በማላውቅበት ጭንቅላቴ ገብተው የነሱ ተከታይ አደረጉኝ አለ ገብረመድህን። በወቅቱ ማገብት በኋላም ተሀህት ከዚያም ህወሀት፡ እስካሁንም ድረስ ትግላቸው በሶስት ዋና ዋና መርሆች ላይ የተመሰረተ ነበር። ኤርትራን ማስገንጠል ወይንም የኤርትራን ቅኝ ግዛትነት መቀበል። የቀይ ባህር የኢትዮጵያ አካል አለመሆን መቀበልና አማራውን ጠላት አድርጎ መቀበል። ሶስተኛውን ረሳሁት። ስለዚህ ከመጀመሪያውም ሕወሀት ኢትዮጵያን ለመበታተን ኤርትራን ለማስገንጠል የተፈጠረ ቅጥረኛ ድርጅት ነው ይለናል ይህ ሰው። ከኢትዮሚድያው አብርሃ በላይ ጋር ይስማማሉ እዚህ ጋር። አብርሀም ይሄንን ነው የሚለው [http://ecadforum.com/ECADF_VIDEO.html](http://ecadforum.com/ECADF_VIDEO.html) ።

**<u>ስለኢኮኖሚ ምንጫቸው ስለዓላማቸው ተጠየቀ።</u>**

ገብረመድህን አርአያ እንዳስቀመጠው፤ ባጭሩ የሕወሀት የኢኮኖሚ ምንጭ ዘረፋ ነው። ሕወሀት መጀመሪያ የትግራይ ዜጎችን አስሮ እየገረፈ ይዘርፍ ነበር። ጎን ለጎን አማራው የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው ብሎ ተነሳ። ኤርትራም ቀይ ባህርም የኢትዮጵያ አካል አይደለችም ብሎ ተዋጋ። በዚህና በሌሎችም ምክንያት ሕወሀት በትግራይ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። በዚህም ምክንያት ብዙ የትግራይ ኢትዮጵያዊያን ተገድለዋል። አቶ ገብረመድህን ብዙ ስም ጠራ፡ እነ ከቡር ፊታውራሪ ...። እነ ደጃዝማች እከሌ። እነ ክቡር ደጃዝማች እንቶኔ። ብዙ የላይኛውን አማራውን ጠላት አድርጎ የመነሳትና ኤርትራን የማስገንጠል የህወሀት አላማ የተቃወሙ የትግራይ ኢትዮጵያዊያን ተገድለዋል። መቼም ታሪክ ስለሆነና አቶ ገብረመድህን ስላለው ላንሳው እንጂ፡ ዛሬ የኤርትራ እጅ እንደሚያስፈልገን የማምነው ሰው ይሄንን መዘገብ አልነበረብኝም። ግን እሱ አቶ ገብሬ አለ።

ስዬ መጣብኝ። ስዬ አብርሃና ገብረመድህን አርአያን በሁለት የተለያዩ ቅርንጫፎች ላይ የሚያስቀምጥ ነገር ብዙ ነው ከዚህ ቃለ ምልልስ እንደተረዳሁት። የዛሬ ዓመት አቶ ስዬ ከእስር እንደተፈታ ከዚያም በኋላ በተካፈለባቸው ስብሰባዎች ላይ ሲናገር አደምጫለሁ። ሌሎች ስለሱ የጻፉትንም ተመልክቻለሁ። ስዬ ፍንክች አላለም። ምንም ሀጢያት ሰራን አይልም። ገብረመድህን ግን እኔ ሀጢያተኛ እያለ ንስሀ ይገባል። አሁንም ስዬ በመድረክ በኩል ከአንድነት ጋር ወግኖ በመስራት ሕወሀትን ለመደምሰስ ይረዳናል ብዬ ብመኝም ልክ እንደኤርትራው ጉዳይ፡ የተባለውን እንደተባለ ከማቅረብ አልቦዝንም። ለነገሩ ይሄ አቶ ስዬን ምላሽ እንዲሰጡ ያነሳሳ ይሆናል እንጂ አይጎዳም።

ቄል፡ ገብረመድህን አርአያና ስየ አብርሀ በሁለት ዓለም ውስጥ ያሉ፡ አንዱ ባውሮፓ አንዲ በኢትዮጵያ፡ በተለያየ ምክንያት ከህወሀት የተገለሉ ወይንም የወጡ ሰዎች ናቸውና፡ ባንድ አይነት ቋንቋ እንዲነጋገሩ ወይንም እንዲመሰክሩ መጠበቅ የለብንም። ግን ልዩነታቸው እጅግ በጣም የተለያየና የሰማይና የምድር ያህል የሰፋ ሆነ። አንዱ ሕወሀትን በሀጢያት ተጸንሶ በሀጢያት ያደገ በሀጢያትም ህይወቱን የሚገፋ የመርገምት ድርጅት ያደርገዋል። አንዱ ደግሞ፡ አቶ ስዬ፡ ሕወሀትን በርግጥም ለቅድስና የቆመ፡ ነገር ግን በሀጥአን የተነጠቀ የቅድስና ድርጅት ያደርገዋል። ለስዬ ሕወሀት ጥቂት ሰዎች ከተወገዱ መታደስ የሚችል ምንም ወንጀል ያልፈጠመ ድርጅት ነው። ለግረመድህን ደግሞ ወያኔ፡ ለፍርድ መሰቀል ያለበት የጥፋት ድርጅት ነው። አንዳንዱ የአቶ ገብረመድህን ምስክርነት ለኔ ራሱ የሚዘገንን ነው። አገር የወጉ። አገር የሸጡ። ህዝብ ያስጨረሱ። ህዝብ ያደሙ። ወገን በረሀብና በመሳሪያ የፈጁ ያደርጋቸዋል ገና ሲፈጠሩም።

የጋሽ ገብሬ ምስክርነት ይመች ነበር። ማንም ሊያደምጠው ይገባል።፡የምግባረ ሰናይ ድርጅት ያቋቋምነው በ1975 ነው አለ። ከዚያ በፊትም በኋላም ግን እንዘርፍ ነበር። እስኪ አቶ ገብረመድህን ሲናገር እንስማው። "እኔ ያኔ ሱዳን ውስጥ እርዳታ የመቀበሉንና ገንዘብ የመቀበሉን ስራ እሰራ ነበር። ብዙ ፈረንጆች ይመጡ ነበር። እርዳታ ለመስጠት። ኋላ ላይ አለቃዬ ስብሀት ነጋ ጠራኝና ገበሬ ወይንም ነጋዴ መስየ እንድቀርብ አደረገኝ። አንዴ ሀኪም እንድሆንም ተደረግኩ። እኔ ገብረመድህን አርአያ ሀኪም መሀመድ እንድሆን ተደረግኩ። ቁርአንና መቁጠሪያ እንዲሁም ጥምጣም ተሰጠኝ። አንድ ታጋይ ሚስትም ተመርቀልኛል አለ ገብረመድህን። እንግሊዘኛ በፍጹም እንዳልናገር አስጠነቀቁኝ።" ማሽላ መሸጥ ነው የሱ ስራ። "ግን የቀረበው የእርዳታ ገንዘብ መጠንና የማሽላው ብዛት አይገናኝም። ስለዚህስ? ከተከዜ አሸዋ እየተጫነ መጣና ማሽላ እንዲመስል ተደረገ። ከፊት ከፊት ማሽላ በጆንያ። ከኋላ አሸዋ የተሞላ ጆንያ ተቀምጦ፡ አንድ ግዜ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን ሌላ ጊዜ አርባ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ሸጥን" አለ። ይህቺ ናት ጨዋታ። ይህቺ ናት ብልጠት። ብሩን ስብሀትና መለስ ወሰዱት አለ። ከዚህ ምን እንማራለን? ብዙ ነገር። ለምሳሌም።

ሁለት ነገር ታየኝ እዚህ ጋር። ዋናው ነገር ወያኔዎች እየዘረፉና እያጭበረበሩ እያምታቱ ሀብት መሰብሰባቸው ነው። ግን ትንሽም ቢሆን ጠላትን ማድነቅና ከጠላትም መማር አለብን። እንደው ጥሎብን ከጠላት መማር አልለመደብንም እንጂ፡ በዚያን ዘመን ጭንቅላታቸው ይሄንን ያህል ብልጠት ከሰሩ፡ እንደው መድህኔዓለምን ነው የምላችሁ ትንሽም አደነቅኳቸው። ። በዚያ መልኩ ነው ማለት ነው ጄኔራሉንና አገሩን ሁሉ እየገዙ እዚህ የደረሱት ያስብላል። ያ ብቻ አይደለም፡ እኛም እነሱ የደረሱበት ለመድረስ ይሄንን ያህል መጓዝ ይጠበቅብናል ማለትም ይመስላል። አሸዋ እንደ ስንዴ መሸጥ አለብን አይነት ነገር። በሚቀጥሉት ቀናት ስለገብረመድህን አርአያ ሌሎች ምስክርነቶች እጽፍላችኋለሁ። ለምሳሌ እሱን ስለዘገነነውና አሁንም ድረስ ቋቅ ስለሚለው ያልተለወጠ የ1975 የሕወሀት መፈክር። እሱ እንዳለው፡ "To keep the Ethiopians is not benefit, to kill them is not loss" አባባል። ይሄንን እሱ እንዳለው ነው ያሰፈርኩት። ኢትዮጵያውያን በተለይ አማሮቹ ብናቆያቸው አይጠቅሙንም፡ ብናጠፋቸውም አይጎዱንም። "አፈር ያርገኝ" ትላለች እናቴ ስትምል። እኔል ልበላችሁ። እንደወረደ፡ ገብረመድህን አርአያ እንዳለው ነው ያሰፈርኩላችሁ። በዚህ ፖሊሲ እጅግ ከማዘኑና

አሁንም ድረስ ከመጻጻቱ የተነሳ፡ ገብረመድህን ይሄ በዓለም ላይ በየትም የሌለ እንደው በካምቦዲያም ያለጠፈጸመ ጸያፍ ፖሊሲ ነው ይለናል ደግሞ ደጋግሞ።

ስለገብሬና ቃለምልልሱ የምለው ይቀጥላል። እስከዚያው ግን ሙሉ ቃለ ምልልሱን www.ecadforum.com ላይ መጠበቅና ማዳመጥ አለባችሁ። ያልተናገረበት ርእስ የለም። ከሀውዜን እስከ ሱዳን ከአዜብ ጎላ እስከ አብርሀም ያየህ፡ ከዚህ በኋላስ እንዴት መጓዝ አለብን በሚለው ርእስ ላይ ጥሩ ተናግሯል። እንደው ምንም አላውቅም ይላል እንጂ፡ ብዙ ያውቃል፡ ሰውዬው።

ልጅ ተክሌ ነኝ። ቫንኩቨር፡ ካናዳ።

------

ፎቶው የሚያሳየው  አንድ ፈረንጅ ከአንድ "የግል ነጋዴ" 300 ሺ ኩንታል ማሽላ ገዝቶ ብሩን "ለነጋዴው" ማሽላውን ደግሞ ለወያኔዎች ሲያስረክብ ነው። ወያኔዎቹ ደግሞ ብር ቆጠራውን ሲያግዙት ይታያል።  ብሩን ይዞ የሚሄደው "የግል ነጋዴ" እንግዲህ ፈረንጁ ዞር ሲልለት ገንዘቡን ለስብሃት ነጋ ወይም ለመለስ ዜናዊ በስነስርአት ያስረክባል። የገብረመድህን አርአያ ስራም ይኸው ነበር። በሚልዮን የሚቆጠረው ብር የሚረከቡት ስብሃት ወይም መለስ ይሁኑ እንጂ ብሩ የት እንደሚያስገቡት ደፍሮ የሚጠይቃቸው ግን አልነበረም። ባለቤቱ የትግራይ ህዝብ ነው የሚሉለት ኤፈርት (EFFORT) እየተባለ የሚጠራው ወደ 100 የሚጠጉ የንግድ ድርጅቶችንና ፋብሪካዎችን ያቀፈው አዜብ መስፍን የምትቆጣጠረው ድርጅትም ቢሆን  የዛሬ 25 አመት ገደማ "ድርቅን" አመካኝተው ይጠቀሙበት ከነበረው የማፍያ አሰራር የተለየ አይደለም። ፎቶው የተወሰደው ማክስ ፐበርዲ ከፃፈውና በ1985 እ.ኤ.አ. ከታተመው "Tigray – Ethiopia's Untold Story" ከተሰኘው መጽሐፍ ነው። ፎቶ አንሺዋም Kristy Wright ትባላለች። ይህ የፎቶ ማስረጃ የት እንደምናገኘው የተባበሩን የሰብአዊ መብት ተሟጋች ወንድሙ መኮንንን ከልብ እናመሰግናለን፡(ኢትዮሚድያ)

www.ethiomedia.com – a site of alternative news and views